"የቀረውንም ነገር ሳልቆጥር፥ ዕለት ዕለት የሚከብድብኝ የአብያተ ክርስቲያናት ሁሉ አሳብ ነው"2ቆሮ11:28

# <u>በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን!</u>

## ለሁለት ቀናት ከሚያዝያ ፬ እስከ ሚያዝያ ፭ ፳፻፲፩ ዓ/ም / April 12-13 2019 በመካነ ራማ ቅዱስ ገብርኤል የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ሳንሆዜ ካሊፎርኒያ የተደረገው የሀገረ ስብከቱ አጠቃላይ ስብሰባ መግለጫ፤

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን የሰሜን ካሊፎርኒያ ፣ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ለመጀመሪያ ጊዜ ብጹዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የቅዱስ ሲኖዶስ አባል እና በቅድስት ማርያም የኢት/ኦ/ተቤ/ክርስቲያን ሎስ አንጀለስ የበላይ ጠባቂ፣ የሀገረ ስብከቱ ሥራ ዋና አስኪያጅ፣የሀገረ ስብከቱ ዋና ጸሐፊ፣ የመምሪያ ኃላፊዎች፣ ጥሪ ተደርጎላቸው በስብሰባው የተገኙ በአገረ ስብከቱ ሥር የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች፣ የሰበካ ጉባዔ/ የቦርድ አመራሮች፣ የሰንበት ት/ቤት ተወካዮች በተገኙበት በእለቱ በሀገረ ስብከቱ አማካኝነት የቀረቡትን አጀንዳዎችን በስፋትና በጥልቀት በመወያየት በሀገረ ስብከቱ ሥር ላሉት አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ይበጃሉ ያሏቸውን የተለያዩ ውሳኔዎች አሳልፏል።

በመጀመሪያው የስብሰባ እለት ዓርብ ሚያዝያ ፬ ከሰዓት በኋላ ስብሰባው በብጹዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጸሎት እና ቡራኬ የተከፈተ ሲሆን የእንኳን ደህና መጣችሁ ንግግር በሀገረ ስብከቱ ዋና ስራ አስኪያጅ በመልአከ ሰላም ማርዬ ሀጎስ ፣ የመርኃ ግብሩ ቅደም ተከተል ዝርዝር ሁኔታ በሀገረ ስብከቱ ዋና ጸሐፊ በቀሲስ ቡሩክ አልዩ ከተገለጸ በኋላ በመቀጠል በአጀንዳው መሰረት ስለሀገረ ስብከቱ መምሪያዎች የአገልግሎት ግምገማ የመግቢያ ገለጻ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብጹእ አቡነ ቴዎፍሎስ ተገልጾ የእለቱ ስብሰባ በአገረ ስብከቱ ያለውን አደረጃጀት አዎንታዊና አሉታዊ ጎኖች፣ እስካሁን የተሰሩ ስራዎች እና ለወደፊት የታቀዱ እቅዶች በማየት ወደ መጨረሻው የእለቱ አጀንዳ አምርቷል። ስብሰባውም የካህናት ብቻ በመሆኑም በእለቱ አጀንዳ መሰረት የክህነት አገልግሎትን በተመለከተ በሀገረ ስብከቱ ሥር በአሉ አብያተ ክርስቲያናት

- ❖ የአገልግሎት ወጥነት
- ❖ የአበይት በዓላትን ንግሥ አከባበር
- ❖ የምሥጢራተ ቤተ ክርስቲያን አዘገጃጀት እና አቀራረብ
- ❖ የመቅደስ ፣ የቅኔ ማህሌት አገልግሎት እና የቅዳሴ መግቢያ ሰዓት ወጥነት እንዲኖረው ስለማድረግ

በሚሉት ዙሪያ የተለያዩ ውሳኔዎችን አስተላልፏል። የተወሰኑትንም ውሳኔዎች ጽ/ቤቱ በደብዳቤ በቅርቡ የሚያሳውቅ ሲሆን ለተፈጻሚነቱም ሁሉም የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት የበኩላቸውን ድርሻ እንዲወጡ በብጹዕ አቡነ ቴዎፍሎስ አባታዊ አደራና መመሪያ ተሰጥቷል።

ለሀገረ ስብከቱም ይበልጥ መጠናከር እንዲረዳ በማሰብ ሀገረ ስብከቱን ለሶስት ወረዳዎች ማደራጀት እና ለሶስቱም ወረዳዎች የየራሳቸው ሊቀ ካህናት/ጸሐፊ እንዲኖራቸው በጉባኤው የቀረበ ሲሆን ከሰሜን ካሊፎርኒያ ኔቫዳ እና አሪዞና ተወካዮች አማካይነት የቀረቡትን እጩዎች በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ብጹእ አቡነ ቴዎፍሎስ ጸድቋል።

በዚሁም መሰረት፡-

1. የሰሜን ካሊፎርኒያ ወረዳ ሊቀ ካህናት - ሊቀ ጠበብት ሀ/ማርያም ተሾመ ፣ ጸሐፊ - ቀሲስ ምሥራቅ ዱባለ
2. የኔቫዳ ወረዳ ሊቀ ካህናት - መጋቤ ምሥጢር አባ ቴዎድሮስ ፣ ጸሐፊ - ቀሲስ አሰፋ አክሊሉ
3. የአሪዞና ወረዳ ሊቀ ካህናት - መልአከ ገነት ቀሲስ ሰሎሞን ዓለሙ ፣ ጸሐፊ - ዲ/ ዶተር ብዕለጸጋ ጥበቡ

በቅዳሜው ሚያዝያ ፳ ስብሰባም የሰበካ ጉባኤ፣የቦርድ ተጠሪዎች ፣ የሰ/ት/ቤቶች ተወካዮች በጋራ ተሳትፈውበታል። በእለቱም፡-

1. በብጹዕ አቡነ ቴዎፍሎስ ስለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን መዋቅራዊ አስተዳደርና ስለ ሀገረ ስብከቱ አደረጃጀት ጠለቅ ያለ ግንዛቤ የሚያስጨብጥ ጥናታዊ ጽሁፍ ቀርቧል።
2. በመልአከ ሰላም አባ ተስፋ ማርያም ስለ አገልጋይ፣ ተገልጋይ እና አገልግሎት ትምህርት ተሰጥቶ የሀገረ ስብከቱ ልዩ ልዩ የመምሪያ ኃላፊዎች ሪፖርት ተደምጧል። በቀረቡት ሪፖርቶች ላይ ከቤቱ የተለያዩ ጥያቄዎች ቀርበው በመምሪያ ተጠሪዎቹ ምላሽ ተሰጥቶበታል። በእለቱ ተወክለው ከመጡት የቦርድ ኮሚቴ አባላት፣የሰበካ ጉባዔ አባላት፣ የሰንበት ት/ቤት አመራር አባላት ልዩ ልዩ ወቅታዊ እና አሳሳቢ የሆኑ ጥያቄዎችን ምላሽ በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ተሰጥቶበታል።
3. የሀገረ ስብከቱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያናት ሀገረ ስብከቱን ለማሳደግ የታቀዱትን እቅዶች እውን ለማድረግ ስምምነት ተደርሶበታል። በዚህም መሰረት
   1. የወርኃዊ መዋጮ ክፍያ ለሀገረ ስብከቱ ሁሉም አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን ገቢ እንዲያደርጉ የተጣለባቸውንም ኃላፊነት በመወጣት ተግተው እንዲሰሩ
   2. ሁሉም ቤተ ክርስቲያናቸውን ተግተው እንዲጠብቁ
   3. ማንኛውንም መመሪያዎችን ተቀብለው ተግባራዊ እንዲያደርጉ መመሪያ ተሰጥቷል።

የሀገረ ስብከቱን ስብሰባ በማስተናገድ እና አርአያ የሚሆን ተግባር በመፈጸም ስብሰባው ተጀምሮ እስኪፈጸም የደከሙት የመካነ ራማ ቅዱስ ገብርኤል ቤተ ክርስቲያን እና ከርቀት በስብሰባው ላይ ለመገኘት በመኪናና በአውፕላን በመጓዝ የታደሙትን የሀገረ ስብከቱ የመምሪያ ኃላፊዎች፣ በአገረ ስብከቱ ስር የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት አስተዳዳሪዎች፣ የሰበካ ጉባዔ/ የቦርድ አመራር፣ የሰንበት ት/ቤት ተወካዮችን በማመስገን ለወደፊቱ በዚሁ በጎ ተግባር እንዲበረቱ ብጹዕነታቸው አሳስበዋል።

በአጭር ጊዜ ውስጥ ከሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት እና ከመምሪያ ሃላፊዎች ጋር በመተባበር መመሪያ በመስጠት ደከመኝ ሰለቸኝ ሳይሉ ይህንን የመሰለ ታላቅ የመወያያ እና የመተዋወቂያ መድረክ ለመፈጠሩ ምክንያት ለሆኑን ብጹዕ አቡነ ቴዎፍሎስ የሀገረ ስብከታችን ሊቀ ጳጳስ ከፍ ያለ ምስጋና ሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት አቅርቧል። ዛሬም በሀገረ ስብከታችን ያገኘነውን ይህን ዕድል ተጠቅመን የፈረሰውን ገንብተን፣ የተበተነውን ሰብስበን፣ የጠመመውን አቃንተንና አስተካክለን ልዩነታችንን አስወግደን አንድነታችንን አጠናክረን ከፊታችን በርካታ ዐበይት ተግባራት እንደሚጠብቁን በማመን

ለቤተክርስቲያን አገልግሎት ከመቼውም ጊዜ በበለጠ በመነሳሳት በየአጥቢያችን ያሉትንም ምዕመናን በማስተባበር ለመንፈሳዊ ጥንካሬ እና ለቤተክርስቲያን እድገት የበኩላችንን አስተዋጽኦ ያለመሰልቸት እንድናበረክት ሀገረ ስብከቱ አሳስቧል። በመጨረሻም የሀገረ ስብከቱ ስብሰባ ማጠቃለያ ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን ዓበይት ጉዳዮች በመግለጫ መልክ በማውጣት ለህዝብ ይፋ እንዲሆን በመወሰን ስብሰባው በብጹዕ ሊቀ ጳጳስ አቡነ ቴዎፍሎስ ጸሎት እና ቡራኬ ተጠናቋል።

ወስብሐት ለእግዚአብሔር!

በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን
የሰሜን ካሊፎርኒያ ፣ ኔቫዳ እና አሪዞና ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት
ሎስ አንጀለስ ካሊፎርኒያ
ሚያዝያ ፫ ፳፻፲፩ ዓ/ም.